ር.ሊ.ጳ. ፍራንቸስኮስ

# FRATELLI TUTTI

በሚል አርእስት ይፋ ያደረጉት

በወንድማማችነት እና በማህበራዊ ወዳጅነት ላይ ያተኮረ ጳጳሳዊ መልእክት

## ስለምን ይናገራል?

"Lumen fidei" (እ.አ.አ 2013) እና "Laudato si′ (እ.አ.አ 2015) በሚል አርእስት ለንባብ ካበቋቸው በመቀጠል በሦስተኛ ደረጃ ይፋ የሆነ ጳጳሳዊ መልእክት ነው።

ተፈርሞ ይፋ የሆነው እ.አ.አ በጥቅምት 03/2020 ዓ.ም አዚዚ በሚባል የጣሊያን ከተማ ውስጥ ነው።

## በምን ላይ የተመሠረተ ነው?

- ወንድማማችነት እና ማህበራዊ ወዳጅነትን በተመለከተ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን እያሳሰባቸው የመጡትን ጥያቄዎች የተመለከተ ነው።
- ጳጳሳዊ መልእክቱ እ.ኤ.አ. በየካቲት ወር 2019 ዓ.ም ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሱ እና ታላቁ ኢ.ማም  አህመድ አል-ታይብ 'ሰብዓዊ ወንድማማችነት ለዓለም ሰላም እና አብሮ ለመኖር' በሚል አርእስት በጋራ በተፈራረሙት ሰነድ ላይ ያጠነጠነ ነው።

## መለእክቱ ማንን ይመለከታል?

ይህንን አስተንትኖ ለሚቀበሉ ሰዎች ሁሉ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ለማስገንዘብ የቀረበ ጥሪ ነው።

## ጳጳሳዊ መልእክቱ የተዋቀረው እንዴት ነው?

- 'ሁላችንም ወንድማማቾች' ነን የተሰኘው ጳጳሳዊ መልእክት አጠቃላይ መግቢያ አካቶ 8 ምዕራፎችን የያዘ ነው።

**መግቢያ**
**ምዕራፍ I.** በተዘጋ ዓለም ላይ ያንዣበበው ጥቁር ጨለማ
**ምዕራፍ 2.** በመንገድ ላይ ያለ አንድ እንግዳ
**ምዕራፍ 3.** ክፍት የሆነ ዓለም ለወደፊቱ እንደ ሚመጣ ማሰብ እና እንዲመጣ መሳተፍ
**ምዕራፍ 4.** ለዓለም ሁሉ የተከፈተ ልብ
**ምዕራፍ 5.** የተሻሉ የፖለቲካ ዓይነቶች
**ምዕራፍ 6.** ውይይት እና ወዳጅነት በማሕበረሰብ ውስጥ
**ምዕራፍ 7.** የታደሰ የመገናኛ መንገዶች
**ምዕራፍ 8.** በአለማችን ውስጥ ወንድማማችነትን በማገልገል ላይ የሚገኙ ሐይማኖቶች

## ምን ዓይነት ሐሳቦችን ያቀርብልናል?

- ወንድማማችነት እና ማህበራዊ ወዳጅነት ላይ ትኩረቱን ያደረገ ጳጳሳዊ መልእክት ነው።
- የወንድማማችነት ፍቅር ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው መመሪያ እንደ ሆነ ይገልጻል።
- ዓላማው የወንድማማችነት እና ማህበራዊ ወዳጅነት አዲስ ራዕይ ማምጣት ነው።
- እንደ ሰብዓዊ ቤተሰብ አንድ አካል መሆናችንን ተረድተን አብረን የምንጓዝ መንገደኞች እንድንሆን ያበረታታናል።

## ርዕሱ የተወሰደው ከየት ነው?

- 'ሁላችንም ወንድማማቾች ነን' ከአዚዚው የቅዱስ ፍራንቸስኮስ ማሳሰቢያዎች የተወሰደ ነው።
- ቅዱሱ አገላለፁን የተጠቀመው በወንጌል ጣዕም የታወደ የሕይወት መንገድ ለማመልከት ነበር።
- ቅዱስ ፍራንቸስኮስ ሁሉም ወንዶችና ሴቶች መልካምድር እና ርቀት ከሚያስከትሉት መሰናክሎች ባሻገር ወደ ሚገኘው ፍቅር እንድሄዱ ይጋብዘናል።

**የክርስትና እምነት ተከታዮች ሕብረት ጸሎት**

"መንፈስ ቅዱስ ሆይ ና፣ በምድር ላይ በሚገኙ በሁሉም ሕዝቦች ላይ አንጸባርቀህ፣ የተለያየ ዓይነት የፊት ገጽታ ያላቸው፣ በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የተወደደ አንድ ስብዕና ያላቸው ሰዎች ሁሉ አስፈላጊ እና ጠቃሚ መሆናቸውን በአዲስ መልክ እንድንረዳ፣ ፣ ውበትህን አሳየን"።

**አሜን**

ር.ሊ.ጳ. ፍራንቸስኮስ

# FRATELLI TUTTI

በሚል አርእስት ይፋ ያደረጉት

በወንድማማችነት እና በማህበራዊ ወዳጅነት ላይ ያተኮረ ጳጳሳዊ መልእክት


## በተዘጋ ዓለም ላይ ያንዣበበው ጥቁር ጨለማ

ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቸስኮስ በአለማችን ውስጥ ሁለንተናዊ የወንድማማችነትን እድገት የሚያደናቅፉ አዝማሚያዎች እንዳሉ ተመልክተዋል።

**“ልዑላዊ የሆነ ማሕበረሰብ ጎረቤታሞች እንድንሆን አድርጎናል፣ ነገር ግን ወንድማማቾች እና እህተማማቾች አላደረገንም”።**

### በተዘጋው ዓለም ላይ የተጋረጠውን ጥቁር ጨለማ እንዴት ልብ ማለት እንችላለን?

- በኅብረተሰቡ ውስጥ ተስፋፍቶ የነበረው ተስፋ መቁረጥ እና የተነሳሽነት መዳከም
- መወያየትን እና አብሮ መኖርን የሚያደናቅፉ ከፍተኛ ልዩነቶች
- በቀላሉ “መስዋዕት” ተደርገው የሚጣሉ እና የተወገዱ ሰዎች።
- መብቶች በእኩለንት አለመከበር እና አዳዲስ የባርነት ዓይነቶች
- የሥነ ምግባር ብልሹነት እና የመንፈሳዊ እሴቶች መዳከም



**ዛሬ ብልጣብልጥ በሆነ መልኩ ጫና መፍጠር የሚችሉ**

**ዲሞክራሲ** ነጻነት ፍትህ ሕብረት

እነዚህን ተግዳሮቶች ለመጋፈጥ ፍራቴሊ ቱቲ (ሁላችንም ወንድማማቾች ነን) የተሰኘው ሐዋርያዊ መልእክት አጥብቆ የሚናገረው
**“መንዝ ያለብን መንገድ የመቀራረብ እና የመገናኘት ባህል ነው ”።**

**እግዚአብሔር የተትረፈረፈ የመልካምነትን ዘር መዝራቱን ቀጥሏል።**

**መልካምነት ከፍቅር ፣ ከፍትህ እና አብሮነት ጋር በእያንዳንዱ ሰው እና በየቀኑ መከናወን አለበት።**

**ተስፋ አድማሳችንን ከሚገድበው ከማንኛውም የግል ምቾት ባሻገር የሚመለከት ሲሆን ለታላላቅ ሃሳቦች ክፍት እንድንሆን ያደርገናል።**

ር.ሊ.ጳ. ፍራንቸስኮስ
FRATELLI TUTTI
በሚል አርእስት ይፋ ያደረጉት
በወንድማማችነት እና በማህበራዊ ወዳጅነት ላይ ያተኮረ ጳጳሳዊ መልእክት

# በመንገድ ላይ ያለ አንድ እንግዳ

**በደጉ ሳምራዊው ምሳሌ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ገጸ ባህሪያት እነማን ናቸው?**

- ወንበዴ የሆኑ ሰዎች
- ገለል ብለው ያልፉ ሰዎች
- የቆሰለው እና በሞት አፋፍ ላይ የሚገኘው ሰው

**በእዚህ ሁኔታ ውስጥ ‘ሁላችንም ወንድማማቾች ነን’ የተሰኘው ጳጳሳዊ መልእክት የሚጠይቀን ነገር?**

?

እንግዲህ ከእነዚህ ሰዎች መካከል ለየት አድርገህ የምትመለከተው ሰው የተኛው ነው? ባልንጀራህስ ማነው?



“ወዳጆቻችን ለእኛ ቅርብ የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው ብለን እንዳንወስን እና ይልቁንም እኛ ራሳችን ለሁሉም ሰዎች ወዳጅ መሆን እንደ ሚገባን ኢየሱስ ያስተምረናል።

## ዛሬ የደጉ ሳምራዊው ታሪክ ተደግሟል

1. የራሳችንን ግድየለሽነት ለመረዳት ቁርጠኛ መሆናችንን ወይም ገዳይ መሆናችንን እንድናረጋግጥ የቀረበ ጥሪ ነው።
2. ህብረተሰቡ ሌሎችን በተለይም አቅመ ደካሞችን ችላ ወደ ማለት አዘንብሏል።
3. ማኅበራዊ መገለልን ዓለም ይፈቅዳል ያበረታታል።
4. በማህበራዊ እና በፖለቲካዊ መስኮች የግድየለሽነት መንፈስ እየተመለከትን ነው።

**የቆሰሉ ማህበረሰብ ክፍሎችን መልሰን በማቋቋም ረገድ ንቁ ተሳትፎ እንድናደርግ ‘ሁላችንም ወንድማማቾች ነን’ ጥሪ ያቀርብልናል።**

የተቸገረ ወንድም ወይም እህት ከየትም ይምጣ ከየት ፍቅር አይገደውም፣ሁሉን ያስተናግዳል።



**እንድንለያይ ያደረጉንን ሰንሰለቶች ፍቅር ይበጣጥሳል፣ በእርሱ ምትክ ድልድዮችን ይገነባል።**

በመንገድ ዳር ቆስሎ የተኛውን ሰው ስታይ በሌላኛው በኩል አልፈ ትሄዳለህ? ወይስ ቆም ብለህ ልትረዳው ትሞክራለህ?

በብዙ ሥቃይና መከራ ውስጥ የእኛ ብቸኛው መንገድ ሊሆን የሚገባው የደጉ ሳምራዊውን ምሳሌ መከተል ነው።

ር.ሊ.ጳ. ፍራንቸስኮስ

# FRATELLI TUTTI

በሚል አርእስት ይፋ ያደረጉት

በወንድማማችነት እና በማህበራዊ ወዳጅነት ላይ ያተኮረ ጳጳሳዊ መልእክት

## ለሁሉም ክፍት የሆነ ዓለም ለወደፊቱ እንደ ሚመጣ መመኘት እና እውን እንዲሆን መጣር።

**ኢየሱስ "ሁላችሁም ወንድማማቾች እና እህተማማቶች ናችሁ" ብሎናል።** (ማቴ 23 8)

### ዓለም አቀፋዊ የወንድማማችነት ጥሪ ግልፅነትን ይጠይቃል።

- የሰው ልጆች ምልአት የሚያገኙት ከልብ በመነጨ መልኩ ራሳቸውን ለሌሎች ሲያቀርቡ ብቻ ነው።
- ፍቅር ሌሎችን መቀበል እና ከእኛ ባሻገር ያሉትን ሰዎች ለመድረስ የበለጠ ችሎታ እንዲኖረን ያደርጋል።
- ድንበሮችን ማለፍ የሚችል ፍቅር "በማህበራዊ ወዳጅነት" ላይ የተመሠረተ ነው።



## መልካም ነገርን ማራመድ ማለት የሰውን ልጅ እድገት የሚያፋጥኑ እሴቶችን ማራመድ ማለት ነው።

### ይህ እንዴት ሊሳካ ይችላል?

- ከማህበረሰብ አንፃር በማሰብ እና በመተግበር።
- የድህነትና የኢፍታዊነት መዋቅራዊ መንስኤዎችን በመዋጋት።
- ክልላዊ መንግሥት በቦታው ተገኝቶ ንቁ እንዲሆን በመጠየቅ እና ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑት ሰዎች እገዛ እንዲያደርግ በማድረግ።
- ማንም እንዳይገለል ዋስትና በመስጠት።
- በአለም አቀፍ ደረጃ የአብሮነትና የአገልጋይነት ስነምግባር ላይ የተመሠረተ እውነተኛና ዘላቂ ሰላም በማስፈን።

**[ እያንዳንዱ ሰው ዋጋ ያለው እና በክብር የመኖር መብት አለው። ]**

# ለዓለም ሁሉ የተከፈተ ልብ

## ለዓለም አቀፍዊ ወንድማማችነት የሚጠቅሙን እርምጃዎች የተኞቹ ናቸው?


1. ስደተኞችን እና ተገልለው የሚገኙትን ሁሉ መቀበል ፣ መጠበቅ ፣ ማስተዋወቅ እና ማዋሃድ።

2. በዘመናችን ሁላችንም አንድ ላይ ድነናል ወይም ማንም ሰው አልዳንም የሚለውን የበለጠ መገንዘብ።

3. የሁሉም ህዝቦች ልማት የሚደግፍ ዓለም አቀፍ የሕግ ፣ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ስርዓት መዘርጋት።

### በነጻ የተሰጠን ነገር ምንድነው?

- አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ መልካም ነው ምክንያቱም ነገሮች በራሳቸው መልካም ስለሆኑ።
- ለግል ጥቅም ወይም ወሮታ ባለማሰብ እርምጃ መውሰድ።
- ምንም እንኳን ይህ ወዲያውኑ ተጨባጭ ጥቅም ባያስገኝልንም አንኳን እንግዶችን መቀበል ይገባል።



የተለያዩ የዓለማችን ሀገሮች ትክክለኛ እሴታቸው የሚለካው ራሳቸውን የትልቁ የሰባዊ ቤተሰብ አካል አድርገው በመቁጠር ላይ የተመሰረተ የማሰብ ችሎታ ላይ ነው። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በነፃ ይሰጣል።

### እያንዳንዱ ጤናማ ባህል በተፈጥሮው ለሁሉም ክፍት እና እንግዳ ተቀባይ ነው

አእምሯችንን እና ልባችንን መከፈት ከእኛ ልዩ የሆኑ ሰዎችን ለመረዳት ይረዳናል።

አለም አቀፋዊ በሆነ ህብረት እያንዳንዱ የሰብስዊ ቡድን የራሱ የሆነ ውበት እንዳለው የገነዘባል።

የሰው ልጆች ውስን ፍጥረት ቢሆኑም እንኳ ገደብ የለሽ ናቸው።

ዓለማቀፋዊ ቤተሰብ መሆናችንን ከተረዳን ለባልንጀሮቻችን ራሳችንን መክፈት አንችላለን።

# የተሻሉ የፖለቲካ ዓይነቶች

**“በማንኛውም ሕግ ውስጥ ኢየሱስ ያስተማረው የግብረ ሰናይ አገልግሎት ሊካተት ይገባዋል” !** (ማቴ 22፡36-40)

## የተሻለ የፖለቲካ ዓይነት ምንድነው?

- የጋራ ጥቅምን እውነተኛ በሆነ መልኩ የምያራምድ።
- ድምጽ ለማግኘት ብቻ የማይጥር።
- ሰብዓዊ እድገት እንዲመጣ እንደ መንገድ ሆኖ የሚያገለግል።
- ብዙሃኑን ያካተተ ምርታማነት እና የንግድ የፈጠራ ችሎታ እንዲኖር የምደግፍ የኢኮኖሚ ዓይነት የምያስተዋውቅ።
- አርቆ አሳቢ እና አዲስ፣ አጠቃላይ እና ሁለገብ ውይይት ማድረግ የምችል።

**ፍራቴሊ ቱቲ (ሁላችንም ወንድማማቾች ነን) በመልእክቱ በጎ አድራጎት ማድረግ የሚችል ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ቅደም ተከተል እንዲኖር ጥሪ ያቀርባል።**

- ሁሉም ወደ ተጠራበት ወደ ፍቅር ስልጣኔ እንዲራመድ ማድረግ።
- ማንም ሳይገለል የሰው ልጆች ሁሉ ወንድም እና እህቶች እንደ ሆኑ አድርጎ መገንዘቡ።
- በጎ አድራጎት የእውነት፣ የአእምሮ እና የእምነት ብርሃንን ይፈልጋል።



**ማህበራዊ በጎ አድራጎት አንድ የሚያደርገን ማሕበራዊ ልኬት እንዲኖር በማድረግ የጋራ ጥቅምን እንድንወድ እና ለሁሉም ሰዎች መልካም ነገር እንድንሻ ያደርገናል።**

**እያንዳንዱ ሰው ክቡር በመሆኑ የተነሳ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የእኛ ፍቅር እና አክብሮት ይገባዋል፣**

ቢያንስ አንድ ሰው የተሻለ ኑሮ እንዲኖር መርዳት ከቻልኩ ፣ ቀድሞውኑ ህይወቴን መስዋእት አድርጌ መስጠቴን የሚያረጋግጥ ነው ”።

## ውይይት እና ወዳጅነት በማሕበረሰቡ ውስጥ።

# “ውይይት” ማለት ምን ማለት ነው?

- እርስ በእርስ ለመተዋወቅ እና ለመረዳዳት የጋራ መግባባትን ለማምጣት በመፈለግ መቅረብ
- መናገር
- ማዳመጥ
- መመልከት



### በግንኙነት ባህል መሰረት

ጥቅም የሌለው ማንም ሰው እንደሌለ እንዲሁም ከሁሉ በላይ የሆነ ማንም ሰው እንደሌለ አንዳችን ከሌላው መማር እንችላለን።

### ውይይትን የሚያበረታታ የብዙኃን ማህበረሰብ

1. በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የሌሎችን ክብር አይነካም።
2. ልዩነቶችን ያዋህዳል ፣ ስለሆነም እውነተኛ እና ዘላቂ ሰላም ያረጋግጣል።
3. የወዳጅነት ድባብን በመጠበቅ ሌሎች ሰዎች እራሳቸውን የመሆን መብታቸውን ይቀበላል።

### ውይይት ከማድረግ የሚያግዱ አመለካከቶች ወይም ድርጊቶች የትኞቹ ናቸው?

- ማንኛውንም ጥቃቶች ለምሳሌ በማህበራዊ አውታረመረቦች ላይ ልናሳያቸው እንችላለን።
- አህዳዊ በሆነ መልኩ ሌሎችን ማዳመጥ።
- በፍጥነት ሌሎችን ማዋረድ።

ትክክለኛ ማህበራዊ ውይይት የሌሎችን አመለካከት የማክበር ችሎታን ያካትታል።

# የታደሰ የመገናኛ መንገድ

## ወደ ሰላም በሚወስደው ጎዳና ላይ የታደሰ የግንኙነት ሂደቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው


- በእውነተኛ እርቅ ውስጥ።
- የእያንዳንዱን ሰው ግለሰባዊነት በማይክዱ የጋራ እቅዶች ውስጥ።
- የሁሉም ሰዎችን ክብር በመገንዘብ፣ በመጠበቅና በማክበር።
- ለድሆች ፣ ለተፈናቀሉት እና ለተገለሉ ሰዎች አማራጭ መፈለግ
- የይቅርታን ትርጉም በመረዳት እና በማድነቅ።

**ኢየሱስ ዓመፅን ወይም አለመቻቻልን በጭራሽ አላበረታታም።**

**ቅዱስ ወንጌል** “ሰባ ጊዜ ሰባት” **ይቅር እንድንል ይነግረናል** (ማቴዎስ 18፡22)

## እውነተኛ ይቅርታ እና እውነተኛ እርቅ

- በግጭት ውስጥ የተገኙ እና በውይይት የተፈቱ ናቸው።
- ከጠላት እና የእርስ በእርስ ጥላቻ መራቅ።
- በፍትህ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ልዩነቶችን በሐቀኝነት ለመወያየት ሁኔታዎችን ማመቻቸት።
- መርሳት ወይም አለመቀጣት ማለት አይደለም።
- የበቀል አዙሪት ውስጥ አለመውደቅ።



“በፖለቲካ አስተሳሰብ ፣ በቋንቋ ፣ በባህል እና በሃይማኖት ምክንያት የሚፈጠሩ ልዩነቶችን እናሸንፍ ዘንድ ከወንድሞቻችን እና እህቶቻችን ጋር ለመገናኘት ልባችንን እንዲያዘጋጅ እግዚአብሔርን እጠይቃለሁ”

**ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቸስኮስ**

ር.ሊ.ጳ. ፍራንቸስኮስ

FRATELLI TUTTI

በሚል አርእስት ይፋ ያደረጉት

በወንድማማችነት እና በማህበራዊ ወዳጅነት ላይ ያተኮረ ጳጳሳዊ መልእክት

# በዓለማችን ውስጥ ወንድማማችነት እንዲፈጠር በማገልገል ላይ የሚገኙ ሐይማኖቶች

## እርስ በእርሳችን በሰላም መኖር የምንችለው ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ስናውቅ ብቻ ነው።

የተለያዩ ሃይማኖቶች ወንድማማችነትን ለመገንባት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።

እግዚአብሔርን መፈለግ እርስ በርሳችን አብረን የምንጓዝ ወዳጆች፣ በእውነቱ ወንድማማቾች እና እህታማማቾች እንድንሆን ይረዳናል።


የሃይማኖት ነፃነት እና የህሊና ነፃነት መካድ የሰው ልጅን ለድህነት ያጋልጣል።

## ቤተክርስቲያን እናት ነች ምክንያቱም በሮች የተከፈቱባት ቤት ናትና :

1. ድልድዮችን ትገነባለች
2. ግድግዳዎችን ታፈርሳለች
3. የእርቅ ዘሮችን ትዘራለች።

## በሃይማኖቶች መካከል የሰላም ጉዞ እንዲኖር ማድረግ ይቻላል

- ነገሮችን በእግዚአብሔር እይታ መንገድ መመልከት የመነሻው ነጥብ መሆን አለበት፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር በልቡ ያያልና።
- አመፅ መሠረታዊ በሆኑት ሃይማኖታዊ እሴቶች ውስጥ መሠረት የለውም።
- ቅን እና ትሑት የሆነው የእግዚአብሔር አምልኮ ለሕይወት ፣ ለክብር እና ለነፃነት አክብሮት ይሰጣል።



**የሃይማኖት መሪዎች አሸማጋዮች እና ሰላምን ለመገንባት ለመተባበር እውነተኛ “የውይይት ሰዎች” እንዲሆኑ ተጠርተዋል።**

## የተለያዩ የክርስትና እምነት ተከታዮች ሕብረት ጸሎት

የቅድስት ሥላሴ ፍቅር በመለኮታዊ ሕይወት ጥልቅ ኅብረት ውስጥ የምትገኝ፣
አቤቱ እግዚአብሄር ሆይ ፣
በእኛ ላይ የወንድማማችነት ፍቅር ጎርፍ አፍስስ።
በናዝሬት ቤተሰቡ ውስጥ እና በጥንታዊው የክርስቲያን ማህበረሰብ ውስጥ የታየውን፣
በኢየሱስ ድርጊቶች ውስጥ የተንፀባረቀውን ፍቅር ስጠን።
በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ክርስቶስን ማወቅ እንድንችል፣ እንደ ተሰቀለ፣ እንደ ተሰቃየ እና በዓለም እንደ ተናቀ፣ በእያንዳንዱ ወንድም ወይም እህት ውስጥ እንደ ተነሳ እና አዲስ ጅማሬ እንደሰጠን በማመን እኛ ክርስቲያኖች ቅዱስ ወንጌልን እንድንኖር ጸጋህን ስጠን።
"መንፈስ ቅዱስ ሆይ ና፣ በምድር ላይ በሚገኙ በሁሉም ሕዝቦች ላይ አንጸባርቀህ፣ የተለያየ ዓይነት የፊት ገጽታ ያላቸው፣ በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የተወደደ አንድ ስብዕና ያላቸው ሁሉ አስፈላጊ እና ጠቃሚ መሆናቸውን በአዲስ መልክ እንድንረዳ፣ ፣ ውበትህን አሳየን።"
**አሜን!**